## <u>ሞት ላይቀር ፍርሃት፣አመጽ ላይቀር ምክኒያት!!</u>

**ከዳዊት ተመስገን (ኖርዌ ኦስሎ)**

**03 May 2017**

አገዛዙ ጥርስ የሌለው ውሻ መሆኑን እያወቅን በድዱ እንዲያላምጥ ለምንድነው ጊዜ የተሰጠው?ይህን ሳስብ ትንሽ የአመጹን ጥያቄ አነሳና ፈጥኜ ጥቂት ዘለግ ላለ አፍታ ያለውን ነገር ላስረዳ ግድ ይለኛል።የረጅም ዘመን አምባገነንነት ያስከተለውን የወያኔ ብዝበዛና ጭቆና የተንሰራፋበትን የፖለቲካ ሁኔታ በሰከነ አዕምሮና በተረጋጋ ሁኔታ ሕዝቡ ሲመረምረውና ሲያየው ከቆየ በኃላ በውጤቱ ይህን እርምጃ ለማቀድ የወሰነው።ይህን ስርዓት በሰላማዊ መንገድ መቀየር ማሰብ በሞቱት ኢትዮጵያን ወንድሞቻችን ደም መታጠብ ያህል ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ የድል ባለቤት እስካልሆነ ድረስ ሕዝባዊ አመጽ ተጀመረ እንጂ አልቆመም ረመጡ ተዳፈነ እንጂ እሳቱ አልጠፋም እንደ ሀገራችን ድፎ ዳቦ ዳር ዳሩ ብቻ ነው እየበሰለ ያለው መሃሉ ሊጥ ሆኗል።

አሁን እኮ ብዙ ስራ አይጠበቅብንም ያንን የተዳፈነ እሳት እፍ ብሎ መቆስቆስ እንጂ በአመጽ ላይ ለመቆየት የሚፈለገው ነጻነቷ  የተጠበቀ ዲሞክራሲያዊ ሀገር ለማስጓስ የሚያበቃን የበጎ ምግባር ስንቅ ለማደራጀት ነው።ጎሳዎችን እስካሁን ካሉበት ሁኔታ በባሰ መልኩ ከሚያራርቅ ማናቸውንም ድርጊት መታቀብ ይኖርብናል።በአጠቃላይ ከባዱ እውነታው ወይም ትክክለኛው ግን ለብዙ ዓመታት በውጭውም ሆነ በሀገር ውስጥ ትኩረት ያልተሰጠው ትግል ለኢትዮጵያውያን ያተረፈውና ያስገኘው ነገር ቢኖር እየበዛ የመጣው የመጨቆኛ ሕግና እየጠበበ የመጣው የመኖር መብት ብቻ ነው።

ይህን እውነታ ለወያኔ የጀርባ አጥንት የሆኑት በተለያየ ሃይማኖት ውስጥም ሆነው በንግዱ ማህበረ ዘርፍ እየሰሩ ላሉ ይህን መረዳት ቀላል ላይሆን ይችላል።ምክኒያቱም ልማት ልማት እያሉ ከኃላ ከበሮ ይዘው የሚመቱት እነዚህ ሀገራችን እየተከሰተ ያለው ሁኔታ የዕድገት፣የፍትህና የሰላም ጎዳና ነው የሚሉት የስርዓቱ ዋና ተጠቃሚዎች ብቻ ናቸው።ላብ አደሩንና ብዙኃኑን አይወክሉም።የኢትዮጵያ ሕዝብ ለረጅም ዘመን ኃይል ስለታከለበት በአሁኑ ሰዓት በመኖርና ባለ መኖር መካከል እየተካሄደ ያለው ዕውነታ ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ ተወደደም ተጠላም ሕዝባዊ አመጽን ትተው በሰላማዊ ትግል ተደራድረን ለውጥ እናመጣለን ማለት ለወያኔ ደጀን ወይም በእሳቱ ላይ ውሃ የመጨመር ያህል ነው።ይልቁን የተዳፈነውን እሳት መቆስቆስ ነው የሚያዋጣው እንጂ ወትሮ መልመጥመጥ መቼ ያዋጣል።

ከጠላት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተያይዞ የሀገራችን ባለቤት ስለሚኩንበት ቀን መወያየት እንጂ ኢትዮጵያውያን በአሁኑ ወቅት ከዘረኝነት የጸዳ መንግስት እንዲኖረን ለማድረግ የሰላማዊ ትግሉ ምንም ውጤት እንዳላመጣ በተደጋጋሚ ታይቷል!እየታየም ነው።በዚህ አጋጣሚ ላሳስብ የምፈልገው አመጽ ካለ አሸባሪ መባል መኖሩን ማወቃችን አይቀሬ ነው።ምክኒያቱም መብት፣ፍትህ፣ ነጻነት በሌለበት ቦታ ሁሉ አመጽ እንዳለው ሁሉ በመኖርና ባለመኖር መካከል በምታደርገው ትግል ሁሉ በተጓዳኝ ደግሞ ጠላት አሸባሪ ማለቱ ጀግኖች ኢትዮጵያዊያንን ግልፅ ነው።ለመሆኑ አሸባሪነት ምንድነው?በዚህ ላይ ትንሽ ላክልበት።ብዙውን ጊዜ እኔ ለመግለጽ የምፈልገው ኢትዮጵያን ብዙ ልሂቃን አሏት እኔም ለማሳወቅ ሳይሆን ለማሳሰብ ነው።

ሽብር ማለት እኔ ፈራሁ ከሚለው የላቲን ቃል እንደመጣና ቃሉም ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለው በፈረንሳይ አብዮት ጊዜ መንግስታዊ አሸባሪነትን ለመግለጽ እንደነበር ያመላክተናል።ይህንን ቃል በጥቅም ላይ ያዋሉት ጃኮቢያዊያን የሚባሉት የፈረንሳይ ጽንፈኛ አብዮተኞች ሲሆኑ አላማቸውም ሕዝቡን በማስጨነቅ በሕዝቡ ላይ የበላይነት ማግኘት ነበር።በአሁን ጊዜ  በሀገራችን ኢትዮጵያ እንደሚደረገው ማለት ነው በፈረንሳይ የሽብር ዘመን የሚባለው ጊዜ እ.ኤ.አ ከመስከረም 1793 እስከ ሐምሌ 1794 የቆየ ሲሆን በዚህ ወቅት የአብዮቱ ጠላቶች የተባሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ፈረንሳዊያን እንደተገደሉ ታሪክ ያስረዳል።ብሎም እንደምታውቁት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ በመጠቀም በሀገራችን በአሁን ጊዜ ብዙ ሕዝብ የዚህ ሰለባ ሆኗል።

ሕዝባዊ አመጽን ለማዳፈን እየተሞከረበት እንደሆነ ይታወቃል።ነገር ግን አይችሉም የትኛውም የአምባገነን አገዛዝ ገዥ ነኝ ስላለ ብቻ ወይም አዋጅ ስለታቀፈ እሱ ራሱ ከምንም ነፃ የሚሆንበት ነገር የለም።ለእነዚህ ፈሳሽና፣አላፊ፣ተጋዥ ክስተቶች ትውልዶች ትክክለኛውን የጉዞ ፈለግ የማሰናዳት ወይም ልዩ ቦይ የመቅደድ ሃላፊነት አላባቸው።ጠንካራ ዜጎች ከያሉበት የሚመጡና ሕዝብን የሚያስተባብሩበት ወቅትም ይህ ሰዓት ነው።በነፍስ መፈተኛነት በተጠቀሰው የሕይወት ነውጥ የጊዜው ክፍል ችግሩን ለመጋፈጥ ወይም እንዲሁ ለችግሩ ለመንበርከክ የምንቆምበት መድረክ ከራሳችን አልፎ የሀገርን ሕልውና ይመለከታል።

የኢትዮጵያን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሙሉ ለሙሉ ሊያጠፋን ከተቃረበው የጎሳ ፖለቲካ መታቀብ ይኖርብናል ለመሆኑ ትግሉን ውጤት አልባ ሆኖ እንዲቆይ ለምን ተፈለገ? እንደሚመስለኝ ምክኒያቱ ዘላቂና ጥራት ያለው የትግል  ውጤት መነሻውም መድረሻውም ጥራት ያለው ኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ ነው።ለምን ጠላት ትንፋሽ እንዲወስድ ጊዜ የተሰጠው ምክኒያቱ ምንድነው? የጠላት መግዣው ዋጋ ስንት ነው ቢሉ ባበደሩት መጠን ነው አሉ።ለዚህ ነዋ በአሁን ሰዓት በሀገራችን ውስጥ በተለያየ የሃይማኖት አባቶች ነን የሚሉ ስለ ይቅርታ ስበኩ ተብለው እየሰበኩ ያሉት ይገርማል።ያለፈ ድግስ ማውራት የእለት እራት አይሆንም እያሉን ነው እኮ ጎበዝ የስልጣን ውጤት እንደ ምንዛሪው ነው የሰው ምንነቱ ከሚለካበት መመዘኛ አንዱ በእጁ ላይ ባለው ስልጣን ተጠቅሞ በሚያደርገው ነገር ነው።

እርግጥ ነው ስልጣን ምግባረ ብልሹ ያደርጋል ብዬ አላስብም፣ፍርሃት ግን ምግባረ ብልሹ ሊያደርግ ይችላል። እንደምናውቀው በብዙ በዓለማችን ውስጥ በስልጣን ላይ ያሉትን ሰዎች ስናይ ይህንን ነገር ነው እየተጠቀሙ ያሉት ምክኒያቱም ስልጣኔን አጣለሁ በሚል የፈራ ሰው ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይልም።ምንም ለማድረግ የማይመለስበትን የመምረጥ ሀላፊነት በራሱ ላይ ነው ያለው መራብን የፈራ ስርቆትና ቀማኛነት ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ሁሉ የስልጣን ጥማት ያለውም ሰው እንደዚሁ ነው ጥቃትን የፈራ ቀድሞ ሊያጠቃ ይችላል።ልክ አሁን እንዳለው አመጽ ገና ለገና ይመታል በገና በሚል የኢትዮድያ ህዝብ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን የማይፈልጉ ጎጠኝነትን የሚያራምዱ ከጥንተ ጠላታችን ጋር በማበር ፀረ-ኢትዮድያዊ በመሆን ሳልገፋ ልግፋ በሚል ሃሳብ ኢትዮድያዊ የሆነውን ሁሉ አሳዳጅ ሊሆኑ ችለዋል።የትግል ውጤት የአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን የሂደት ጉዳይ ነው።

በማንኛውም ውጤትን በፈለግንበት የሕይወት አቅጣጫ ካለማቋረጥ ልንራመድ ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማለፍ ጥረት ማድረግ አለብን።ውጤት አንድ ደረጃ ካልደረስኩ አልረጋጋም ማለት ሳይሆን ጉዞውን በመጀመራችንና በሂደት ላይ በመሆናችን መርካትና መረጋጋት ይመስለኛል።በዚህም ዘርፈ ብዙ በሆነ የውጤት ጉዞ ውስጥ መስመር በያዙልን ትግል ዙሪያ በመገስገስ ወደ ኃላ የቀሩትን የትግል ወጤት ደግሞ የበለጠ ለማሻሻል መንገድ በመፈለግ ልንቀጥል ይገባናል።ዘርፈ ብዙ የሆነው የትግል ወጤት ምስጢር ዘርፈ ብዙ የሆነ ጥረትና ትጋት ይጠይቃል።አዎን! በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን እድገት እያሽቆለቆለ ይገኛል።ወጣቱ በስደት ላይ በሞት እያለቀ ይገኛል።ስራ አጥነት ከመቼውም በላይ የከፋ ደረጃ ላይ እየደረሰ ይገኛል።

ኑሮ ተወዶአል።ድሆች መኖር አልቻሉም እያሉ የሚጮኹትን የሰዎችን መንፈስ ሁላችንም ልንከፍለው ይገባል።ያንጊዜ ነው ጩኸቱ ውጤት የሚያመጣው።ያንጊዜ ነው ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የሚባለው ነገር የሚሆነው።እኛ ባይሳካስ በሚል ቅድመ ሃሳብ የተገታን ሳይጀመር የቆምን፣ሳንራመድ የተሰናከልን።ሳንሞክር ደግሞ የከሸፈብን መሆን የለብንም።ውሃ ተመልሶ ወደ ኃላው ቢሄድ(ቢፈስ)፣ዎፎች አለ ክንፍ ቢበሩ፣ቁራ እንደበረዶ ቢነጣ፣ጠላት ወዳጅ ሊሆን እንደማይችል ዕወቅ።ወይራ ጠማማነቱን ቢተው፣ነብር ዥንጉርጉርነቱን ቢለቅ ወያኔ ክፋታቸውን አይተውም።ስለዚህ የተኛህ ንቃ።ለፌ ወለፌ በሚሉ ሆድ አደሮች በእኛ ላይ የሚወረውሩትን የተቃውሞ ድንጋይ የስልጣን መሰረት ለመጣል የምንጠቀምበት የእኛነታችን ውጤት ነው።

ያለምነውን ወይም የጀመርነውን ሕዝባዊ አመጽ መራር ሆኖ ጊዜ ቢወስድም መጀመሪያ ከእኛ የሚጠበቀውን   ሞት ላይቀር ፍርሃት የሚለውን ደጀን ማንገብ ይኖርብናል።እነዚህ ነገሮች እንዲሳኩልን ከፈለግን ካለብን የመውደቅ ፍርሃት   ይልቅ ለውጤት ያለን ፍላጎት መሆን አለበት።በእርግጥ ሰው ሁሉ በሚጋራው የመድረሻ ጉዞ ውስጥ ማንንም የማይምር አንድ ክፉ ችግር አለ።እርሱም የፍርሃት ችግር ነው።

ሁላችንም ቢሆን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የምንፈራቸው ነገሮች አሉ።የመውደቅ ፍርሃት፣ውጤት የማጣት ፍርሃት፣ጀምሮ የማቋረጥ ፍርሃት ነው።ከዚህ ሁሉ የሚጋራንን ፍርሃት የተሰኘውን ተራራ አልፎ ወደ ተፈለገበት ዓላማ ለመዝለቅ ብሎም ወደ ግባችን ለመድረስ ያለን የውስጥ ፍላጎት ካለብን ስጋትና ፍርሃት በብዙ እጥፍ ሊጠነክር ይገባዋል።ግልባጭና ቅጂ ነገር ይዞ ኢትዮጵያዊ ነኝ እያሉ ከመፎከር ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊነትን አንግቦ ውጤት ማጣት ይሻላል።

የወያኔን አምባገነን አገዛዝ በተባበረ ትግል እናስወግዳለን!!

dawitemesgen@gmail.com